# በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት

# ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት

# የሰባት ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ

# (ከ2016- 2022 ዓ.ም)

ጥር/2016 ዓ.ም

ሆሳዕና፣

## ማውጫ


መግቢያ፣ ....... 2
ክፍል አንድ ....... 3
1. አጠቃላይ ገፅታ ....... 3
1.1. የሴክተሩ ተልዕኮ፣ ራዕይ እና እሴቶች ....... 3
1.1.1. ተልዕኮ ....... 3
1.1.2. ራዕይ ....... 3
1.1.3. እሴቶች ....... 3
1.2. የክልሉ አጠቃላይ ገጽታ ....... 3
1.3. የክልሉ አጠቃላይ ገጽታ ....... 3
(ይህ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል አስተዳደራዊ ካርታ የተገኘው ከክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ የቀረ ሰባት አመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ሰነድ ላይ ነው) ....... 5
1.4. ተቋማዊ ገፅታ ....... 5
1.4.1. አመሰራረት ....... 5
1.5. አደረጃጀት ....... 6
1.6. የሰው ኃይል ....... 6
1.7. የሚሰጡ አገልግሎቶች ....... 7
ክፍል ሁለት ....... 9
2. ያለፉት አመታት የሴክተሩ ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ ....... 9
የ10 ዓመቱ (2013-2015 ዓ/ም) ስትራቴጂክ ዕቅድ ግምገማ ከተቀመጡ ግቦች አንፃር ....... 9
ክፍል ሶስት ....... 12
3. የሴክተሩ መሪ ዕቅድ መነሻዎች፣ ዓላማዎች፣ ግቦችና የትኩረት አቅጣጫዎች ....... 12
3.1. መነሻዎች ....... 12
3.2. የዕቅዱ ዓላማ ....... 12
3.2.1. ዋና ዓላማ (General Objective) ....... 12
3.2.2. ዝርዝር ዓላማዎች (Specific Objectives) ....... 12
3.3. የዕቅዱ አስፈላጊነት ....... 13
3.5. የትኩረት መስኮች ....... 13
3.5.1. የተመረጡ የትኩረት መስኮችና ማብራሪያዎች፣ ....... 13
3.6. የዕቅዱ ግቦች ....... 16
4. የሴክተሩ ስትራቴጂያዊ ግቦች ....... 17
5. የሴክተሩ የሰባት ዓመት ዕቅድ የድርጊት መርሃ ግብር ....... 18
ክፍል አራት ....... 20
4. የማስፈፀሚያ ተቋማዊ አቅም ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ....... 20
4.1. የማስፈፀሚያ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ....... 20
4.1.1. መሪ ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ምቹ ሁኔታዎች ....... 20
4.1.2. በዕቅዱ አፈፃፀም ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ሥጋቶች ....... 20
4.2. ስትራቴጂያዊ ዕርምጃዎች ....... 21
ክፍል አምስት ....... 22
5. የፋይናንስ ፍላጎት ....... 22
ክፍል ስድስት ....... 23
6. የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት ....... 23
6.2 የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት ....... 24
7.ማጠቃለያ ....... 25

## መግቢያ፣

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት የክልሉን ህዝብ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ፖለቲካዊና የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመቅረፍና ስርነቀል ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን በመንደፍ እንዲሁም አደረጃጀትና የአሰራር ስርዓትን በመዘርጋትና ተግባራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ህብረተሰቡን በየደረጃው ተጠቃሚ የሚያደረጉ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት የርዕስ መስተዳድር ጽ/ቤትም ተልዕኮውን እና የሚጠበቅበትን ውጤት ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማሳካትና የላቀ አፈጻጸም ለማስመዝገብ የክልሉን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት ያደረገ ዕቅድ በማዘጋጀት ላለፉት ሦስት የስትራቴጂክ ዕቅድ ዓመታት ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

በዕቅዱ የነደፋቸውን የግብ ስኬቶችንም በየጊዜው በመፈተሽ ማሻሻያዎችን ከማድረጉም በተጨማሪ በየዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ የማጠቃለያ ግምገማዎችን በማድረግ ለቀጣይ አመታት አፈጻጸም መሻሻል የሚረዱ አዳዲስ ስልቶችን መንደፍ ተችሏል፡፡ በዚህም ግምገማ የተገኙ ውጤቶች፣ ያልተፈጸሙ ቀሪ ስራዎች፣ የታዩ የአፈፃፀም ውስንነቶች እንዲሁም ለአፈጻጸም ማነቆ የሆኑ ችግሮችና ሊሞሉ የሚገባቸውን ክፍተቶች መለየት ተችሏል፡፡

በመሆኑም በቀጣይ ስትራቴጂክ እቅድ ትግበራ ዘመን (ከ2016- 2022) ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮችን መነሻ በማድረግ፣ ከፌደራልና ከክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ የመጡ አቅጣጫዎችን በመቀበልና አፈጻጸሙን ትርጉም ባለው ሁኔታ መምራት እንደሚገባ በመታመኑ ከዚህ በፊት በ2012 በጀት ዓመት የተዘጋጀውን የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ እንደገና በማሻሻልና በስድስት ክፍል በማዋቀር የቀሪ ሰባት አመታት ዕቅድን በመከለስ እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## 1. አጠቃላይ ገፅታ

### 1.1. የሴክተሩ ተልዕኮ፣ ራዕይ እና እሴቶች

#### 1.1.1. ተልዕኮ

በክልሉ ያሉትን ሰብአዊና ተፈጥሮአዊ ሐብቶች አቀናጅቶ ቀጣይነት ባለው መልኩ ጥቅም ላይ እንዲዉሉ በመምራትና በማረጋገጥ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማትና እድገትን አጠናክሮ በማስቀጠል የክልሉ ህዝብ የልማትና የመልካም አስተዳደር ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ፡፡

#### 1.1.2. ራዕይ

በክልሉ ሰላምና ፀጥታ ተረጋግጦ እና መልካም አስተዳደር ሰፍኖ ዘላቂ ልማትን በማምጣት ህብረተሰቡ ተጠቃሚ ሆኖ ማየት፡፡

#### 1.1.3. እሴቶች

- የህግ የበላይነት መርሀችን ነው ፡፡
- ለተገልጋይ ፍላጎት ትልቅ ዋጋ እንሰጣለን፣
- መቻቻል ባህላችን ነው፣
- አሳታፊነት መለያችን ነው፡፡
- ፍትሐዊነትና ሚዛናዊነት መመሪያችን ነው፡፡
- ብዝሃነታችን ለህብረ ብሄራዊ አንድነታችን መሰረት ነው፡፡

### 1.2. የክልሉ አጠቃላይ ገጽታ

### 1.3. የክልሉ አጠቃላይ ገጽታ

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ 12 ክልሎች እና ሁለት ከተማ አስተዳደሮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ የክልሉን ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ በተመለከተ ከ70 04' እስከ 80 03' ሰሜናዊ ኬክሮስ እና ከ370 20' እስከ 380 60' ምሥራቃዊ ኬንትሮሰ ላይ ይገኛል፡፡ ክልሉን ከሚያዋስኑ የሀገሪቱ ክልሎች አንጻር በሰሜን፣ በምዕራብና በምስራቅ አቅጣጫ ከኦሮሚያ ክልል፣ በደቡብ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል፣ በደቡብ ምዕራብ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ጋር ይዋሰናል፡፡

የክልሉ የቆዳ ስፋት በተመለከተ 1,515,600 ሄ/ር ሲሆን ከአጠቃላይ የኢትዮጵያ የቆዳ ስፋት 1.38 በመቶው የሚይዝ ነው፡፡

የክልሉን ሕዝብ ብዛት በተመለከተ በ1999 ዓ.ም የብሔራዊ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ውጤት (CSA, 2007) መረጃ ፕሮጀክሽን መሠረት በ2015 ዓ.ም የክልሉ ሕዝብ ቁጥር 7,039,772 እንደሆነ ይገመታል፡፡ ይህም ከአገሪቱ አጠቃላይ ህዝብ ብዛት 6.47 በመቶ የሚሸፍን ነው፡፡ ከክልሉ ህዝብ 80.7 በመቶ በገጠር እና ቀሪው 19.3 በመቶ ህዝብ ደግሞ በከተሞች የሚኖር ሲሆን የክልሉ አማካይ የህዝብ ጥግግት 464 ሰዎች በአንድ ካሬ ኪ.ሜ ይኖራሉ፡፡ የክልሉ ሕዝብ አማካይ አመታዊ የዕድገት ምጣኔ 2.9 በመቶ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የዕድገት ምጣኔ በገጠርና በከተማ ሲታይ የገጠር ሕዝብ ዕድገት 2.8 በመቶ ሲሆን የከተማ 4.8 በመቶ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ (ፕላንና ልማት ቢሮ፣ 2016) ፡፡

የክልሉን ስነ-ምህዳር በተመለከተ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በአገሪቱ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም የአየር ንብረቶች ይዟል በሚባል ደረጃ ለኑሮ ምቹ የሆኑ የደጋ፣ የወይና ደጋ እና የቆላ አከባቢዎች ያሉት ሲሆን በሁለት የተራራቁ ጫፎች ያለው የአየር ንብረትም በክልሉ የተለያዩ ስነ-ምህዳር (Ecology) የተፈጥሮ ሀብቶች፣ የተለያዩ የግብርና ሥርዓቶች፣ የአኗኗርና የባህል ብዝሀነት እንዲኖር አድርጓል፡፡ አምበሪቾ፣ ሸንቆላ፣ ዘቢዳር እና ሙጎን የመሳሰሉ ተራራዎች የክልሉ ከፍተኛ ሥፍራዎች ሲሆኑ ዝቅተኛው ሥፍራ ደግሞ በጠምባሮ ልዩ ወረዳ በኦሞ ወንዝ አቅራቢያ ባለው የኦሞ ሸለቆ ጫፍ ከባህር ጠለል በላይ 447 ሜትር ከፍታ ያለው ሥፍራ ነው፡፡


ክልሉ በውስጡ 7 ዞኖችን፣ 3 ልዩ ወረዳዎችን፣ 50 ወረዳዎች፣ 29 የከተማ አስተዳደሮችን እንዲሁም 1,310 የከተማና የገጠር ቀበሌዎችን ያቀፈ ነው፡፡

የክልሉ መንግስት ለህብረተሰቡ ግልጽና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አሳታፊ አሰራርን በማስፈን የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ሊያረጋግጥ በሚያስችል መልኩ ያልተማከለ አሰራርን በመዘርጋት በጀት፣ሥልጣንና የሰው ሃይልን ወደ ታችኛው ዕርከን በማውረድ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

በክልላችን ገጠር አካባቢ የሚገኘው አርሶ አደር ምርትና ምርታማነቱ እንዲጨምር በተከናወኑ ዘርፈ ብዙ ስራዎች ተጠቃሚ እንዲሆን በመደረጉ ኑሮው በመሻሻል ላይ ይገኛል፣ በከተሞችም በተሰሩ የቤቶች ልማት፣ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲሁም ሌሎች ስራዎች ህብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያደርግ ተግባር እየተከናወነ ይገኛል፡፡

በክልሉ የትምህርትን ሥርጭት ተደራሽነት፣ ፍትሀዊነት እና ውጤታማነት የማረጋገጥ ሥራዎች የተከናወኑ ሲሆን በተለይም ሽፋንን በማሳደጉ ረገድ አበረታች ውጤት ተመዝግቧል፡፡ በትምህርቱ ጥራትም ተመሳሳይ ውጤት ለማስመዝገብ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፓኬጆች ተቀርፀው ተከታታይነት ያለው ሥራ በመሠራት ላይ ነው፡፡

በመከላከል ላይ የተመሰረተ የጤና ፖሊሲ በመተግበር እንዲሁም የጤና ተቋማትን በማስፋፋትና በማጠናከር የህብረተሰቡን ጤንነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ ስራ ስራዎች ተከናውነዋል፤ በመከናወን ላይም ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት ዓመታት ህብረተሰቡን የልማት፣ የመልካም አስተዳደርና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ተሳታፊና ተጠቃሚ በማድረግ በክልሉ መንግስት ታቅደው በተከናወኑ ዘርፈ-ብዙ ስራዎች ህዝቡን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡




(ይህ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል አስተዳደራዊ ካርታ የተገኘው ከክልሉ ፕላንና ልማት ቢሮ የቀሪ ሰባት አመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ሰነድ ላይ ነው)

## 1.4. ተቋማዊ ገፅታ

### 1.4.1. አመሰራረት

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት የአስተዳደር ሴክተር በ2015 ዓ.ም በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 70 እና 72 ለመስተዳድር ምክርቤቱና ለክልሉ ርዕሰ-መስተዳድር የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት በአግባቡ ለመወጣት እንዲያስችለው ከክልል እስከ ቀበሌ ድረስ አደረጃጀትና አሰራሮችን በመዘርጋት የክልሉን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ለማፋጠን እና ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ብሎም የተገልጋዩን ህብረተሰብ የልማት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ተቋቁሟል፡፡

ጽ/ቤቱ ከሌሎች በክልላችን ከሚገኙ አስፈፃሚ አካላት በተለየ ሁኔታ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ጽ/ቤት በመሆን ጭምር እንደሚያገለግል በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀፅ

70 እና 72 ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን ይህም ከሌሎች አስፈፃሚ አካላት የሚለየው ዓይነተኛ ባህርይ ነው።

**1.5. አደረጃጀት**

የክልሉን አስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 197/2015 ዓ.ም በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 74(1-5) መነሻነት የሚከተሉት ጽ/ቤቶች ተቋቁመዋል።

በዚሁ መሰረት የርዕሰ-መስተዳድር ጽ/ቤት ተልዕኮውን በዋናነት ለማሳካት በሚያስችሉ ሦስት ጽ/ቤቶች የተደራጀ ሲሆን እነሱም፣

- የርዕሰ-መስተዳድርና የመስተዳድር ም/ቤት ጽ/ቤት
- የአማካሪዎች ጽ/ቤት
- የህግ እና የመልካም አስተዳደር ጉዳዮች ጽ/ቤት ናቸው።

አደረጃጀቱም እንደስራው ስፋት በዞን፣ በልዩ ወረዳ እና በወረዳ እንዲሁም የከተማ አስተዳደሮች ወጥነት ባለው መልኩ በየፈረጃቸው ተደራጅቷል።

**1.6. የሰው ኃይል**

ሴክተሩ ተልዕኮውን በአግባቡ ለመወጣት በሚያስችል መልኩ በስራሂደት ለውጥ ጥናት በተለየው መሰረት እስከታችኛው መዋቅር በትምህርት ዝግጅትና የሥራ ልምድ ብቁ በሆነ የሰው ሀይል የተደራጀ ሲሆን የሰው ሀይሉ ለቀጣይ የዕቅድ ዘመን አፈፃፀም ውጤታማነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይታመናል።

በዚሁ መስረት የሴክተሩን የሰው ሀይል ጠቅላላ መረጃ ለማወቅ ይረዳ ዘንድ ከዚህ በታች በተቀመጠው ሰንጠረዥ በትምህርት ደረጃና በፆታ ለማስቀመጥ ተሞክሯል።

| ተ.ቁ | የት/ደረጃ | ወንድ | ሴት | ጠቅላላ ድምር | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከ5ኛ እስከ 12ኛ ክፍል | 5 | 9 | 14 | ሾፌሮች፣ተላላኪዎችና የፀዳት ሠራተኞች |
| 2 | ሰርተፍኬት | 4 | 6 | 10 | (10+1,10+2,ደረጃ$_1$ እስከ ደረጃ$_4$ |
| 3 | የመጀመሪያ/ባችለር/ ዲግሪ | 3 | 11 | 14 | (BA,BCS,እና LLB) |
| 4 | ማስተርስ ዲግሪ | 12 | 4 | 16 | (MA,MSC, እና LLM) |
| 5 | ዶክተሬት ዲግሪ (PhD) | - | - | - | (PhD) ና ሌላ |
| | ጠቅላላ ድምር | 24 | 30 | 54 | |

## 1.7.የሚሰጡ አገልግሎቶች

### በሴክተሩ የሚሰጡ አገልግሎቶች ፡-

- የአስፈፃሚ ተቋማትን የአጭርና የረጅም ጊዜ የዕቅድ አፈጻጸም የመከታተል፣ የመቆጣጠርና የመገምገም እንዲሁም ለሚመለከተው አካል አቅርቦ የማስወሰን ስራ፣
- ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው የኢኮኖሚያዊ፣ ማኀበራዊና የመሰረተ-ልማት ጉዳዮችን የመመርመር፣ የማጥናት፣ መፍትሔ እንዲያገኙ የማድረግና አፈፃፀማቸውን የመከታተል ስራ፣
- ለዕቅድ አፈጻጸም እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ክፍተቶችን በጥናት የመለየት እና የመከታተል ስራ፣
- ሥርዓተ-ምግብ ተኮር ስትራቴጂዎች፣ ፕሮግራሞች እና መመሪያዎች በምግብና ሥርዓተ-ምግብ ተግባሪ ሴክተሮች እንዲተገበር ማስተባበር፣ ትግበራውን የመከታተልና የመገምገም ስራ፣
- ወረዳን መሰረት ያደረገ ሥርዓተ-ምግብ ተኮር ዝርዝር እቅድ እንዲዘጋጅ እና እንዲተገበር ድጋፍና ክትትል የማድረግና የመገምገም ስራ፣
- በቴክኖሎጂ የተደገፈ የተቀናጀ የሥርዓተ-ምግብ መረጃ ሥርዓት እንዲጠናከር፣ ጠቋሚዎች እንዲለዩ፣ እንዲካተቱና እንዲተገበሩ ተግባሪ ሴክተሮችን የማስተባበር ስራ፣
- ሥርዓተ-ምግብ ተኮር ተግባራት በሴክተሮች ሰነዶች ተካተው መተግበራቸውን የማረጋገጥ ስራ፣
- በሚመለከታቸው የክልሉ ተቋማት የተከናወኑ ወሳኝ ተግባራትን በመለየት የፋይዳ ዳሰሳ ጥናት እንዲከናወን የማስተባበር ስራ፣
- የህግ ታራሚዎች ይቅርታ እንዲያገኙ ያቀረቡትን ጥያቄ ተገቢነት የማጣራት ስራ፣
- የሰብአዊ መብቶች አያያዝና የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እንዲሻሻል የሚያስችል አሰራር እንዲኖር የማድረግ ስራ፣
- በተቋማትና በክልሉ ፍትህ ቢሮ ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ህጎችን የመመርመር እና ለመስተዳድር ምክር ቤት እንዲቀርቡ የማድረግ ስራ፣
- የሌሎች ተቋማትን ረቂቅ ህጎች መሰረታዊ የህግ መርሆዎችን የተከተሉ መሆናቸዉንና አስፈላጊነታቸዉን የማጣራት ስራ፣
- በህግ ጉዳዮች ላይ ለመስተዳድር ም/ቤቱም ሆነ ለርዕሰ-መስተዳድሩ ተገቢውን ሙያዊ አስተያየትና የመፍትሄ አማራጮችን የማቅረብ ስራ፣
- የፍትህ ስርአት ማሻሻያ ፕሮግራም በሚመለከታቸው ተቋማት ተቀናጅቶ ሊተገበር በሚችልበት ሁኔታ መታቀዱንና መከናወኑን በመከታተል ለርዕሰ-መስተዳድሩ ሪፖርት በማቅረብ ግብረ መልስ እንዲሰጥበት የማድረግ አገልግሎት፣
- የመስተዳድር ምክርቤቱን የስብሰባ ሂደቶች በመቅረፀ-ምስል፣ መቅረፀ-ድምፅና በህትመት ሠነዶችን በአግባቡ በመያዝና በመጠበቅ ለሚፈቀድላቸዉ አካላት የማቅረብ ስራ፣

- የመስተዳድር ምክርቤቱን ቃለ-ጉባዔ መያዝ እና የሚተላለፉ ዉሳኔዎች ሚስጢራዊነታቸዉ ተጠብቆ ለሚመለከተዉ አካል ተደራሽ እንዲሆኑ የማድረግ ስራ፣
- ለካቢኔ የሚቀርቡ ጉዳዮች በመስተዳድር ምክርቤት አሰራር ደንብ መሰረት ተገቢውን የጥራት ደረጃ ጠብቀው መቅረባቸውን የማረጋገጥ አገልግሎት፡፡
- የክልሉ መስተዳድር ምክርቤት የሚያፀድቃቸዉን ደንቦችና መመሪያዎች አሳትሞ ለሚመከታቸው አካላት የማሰራጨት ስራ፣
- ከመንግስት መ/ቤቶች ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ለውይይት የሚቀርቡ ሰነዶችና የውሳኔ ሀሳቦችን በተመለከተ የማማከር፣ ድጋፍ የመስጠትና የማስተባበር ስራ፣
- በመስተዳድር ምክርቤቱ ለሚቋቋሙ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ድጋፍ የመስጠትና የማስተባበር ስራ፣
- በዞኖች፣ በልዩ ወረዳዎችና ወረዳዎች የካቢኔ የአሰራር ስርዓት ደንቡን የተከተለ ስለመሆኑ ክትትልና ድጋፍ የማድረግ ስራ፣
- በክልሉ ህገ-ወጥ የሰዎች ዝዉዉርን በመከላከል ዙሪያ በተለያዩ ተቋማት የሚከናወኑ ተግባራትን የመከታተልና የመደገፍ ስራ፣
- ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድርና ምክትል ርዕሰ መስተዳድሮች፣ ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጪ ሀገር ወደ ክልሉ ለሚመጡ ከፍተኛ የመንግስት የሥራ ኃላፊዎች፣ አምባሳደሮችና የአለምአቀፍ ድርጅቶች ተጠሪዎች የፕሮቶኮል ሽፋን የመስጠት አገልግሎት፣
- የሪፎርም ኘሮግራሞች ጉዳዮችን አተገባበር የመከታተል፣ የመደገፍና ግብረ-መልስ የመስጠት ስራ፣
- የመልካም አስተዳደር ፖኬጆች አተገባበርና ዉጤታማነትን በተመለከተ የፋይዳ ዳሰሳ ጥናት የማከናወን ስራ፣
- በየደረጃው የተዋቀሩ የፀጥታ ምክር ቤቶች ኃላፊነታቸውን በአግባቡ በሚወጡበት አግባብ የመደገፍና የመከታተል ስራ፣
- የፀጥታ ሴክተሩ የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ ሊወጣ በሚችለበት አግባብ አፈፃፀሙን የመከታተልና የመደገፍ ስራ፣
- በአጎራባች ክልሎች ድንበር አካባቢዎች የሠላምና የልማት ስራዎች በቅንጅት እንዲከናወኑ የመደገፍ አገልግሎት፣
- ወቅታዊ አጠቃላይ የፀጥታ ሪፖርቶችን በመቀበል፣ በመተንተንና ዕንድምታዎችን ለይቶ ሪፖርት የማቅረብና ግብረ መልስ እንዲሰጥባቸው የማድረግ ስራ፣
- አስተዳደራዊ ቅሬታዎችንና አቤቱታዎችን የመቀበል፣የማጣራትና ዉሳኔ እንዲያገኙ የማድረግ ስራ፣
- የቅሬታና አቤቱታ መንስኤዎች ላይ ጥናት በማካሄድ ዘላቂ መፍትሄ እንዲያገኙ የማድረግ ስራ፣
- በየደረጃዉ የሚገኙ የቅሬታና አቤቱታ መዋቅሮችን የመከታተልና የመደገፍ ስራ፣
- በየደረጃዉ የሚገኙ የቅሬታና አቤቱታ መዋቅሮች ላይ የሚሰሩ ፈፃሚዎችን አቅም የማሳደግ ስራ፡፡

## ክፍል ሁለት

## 2.ያለፉት አመታት የሴክተሩ ዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ

### የሦስት ዓመቱ (2013-2015 ዓ/ም) ስትራቴጂክ ዕቅድ ግምገማ ከተቀመጡ ግቦች አንፃር

ፈጣንና ፍትሀዊ ውሳኔ በመስጠት የተገልጋዩን እርካታ ከማሳደግ አንፃር በተቀመጠው ግብ መሠረት ከአስተዳደራዊ፣ ከፀጥታና ሪፎርም እንዲሁም ከህግ ጉዳዮች ጋር ተያይዘው ለሚነሱ ቅሬታዎች፣ አቤቱታዎችና ጥያቄዎች ፈጣን፣ ፍትሀዊና ውጤታማ አስተዳደራዊ ውሳኔ /ምላሽ/ በመስጠት፣ ለውሳኔ የቀረበውን ጉዳይ ህጋዊ መሰረትና ተገቢነት በማጣራት ለውሳኔ ሰጪ አካል የውሳኔ አስተያየት ከበቂ ማብራሪያ ጋር በማቅረብ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ቅልጥፍና በማረጋገጥ የተገልጋዩን ፍላጎት ከማርካት አንፃር በተሰበሰበ የተገልጋይ አስተያየትና ከባለድርሻ አካላት ጋር በተደረጉ ውይይቶች በ2012 በጀት ዓመት ከነበረው የዕቅድ አፈፃፀም መነሻ 82% በ2015 በጀት አመት ወደ 88% ለማሳደግ ግብ ተጥሎ የዕቅዱን 80.5% ማሳካት የተቻለ ቢሆንም በአለማቀፍ ደረጃ የተከሰተው የኮቪድ ወረርሽኝ፣ ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ በተፈጠሩ የፀጥታ ችግሮችና አለመረጋጋት፣ በየአካባቢው በሚነሱ የመዋቅር ጥያቄዎች ምክንያት ከታችኛው መዋቅር ጋር በተፈጠረ የግንኙነት መላላት ተናቦ ለመስራት አለመቻል፣ በየወቅቱ የኃላፊዎች መቀያየር፣ እንደሴክተር ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች ከተቋሙ የስራ ስፋት አንፃር የደረጃ ማነስ ምክንያት ከፍተኛ ፍልሰት መኖር እና በሌሎችም ችግሮች ምክንያት ግቡን ሙሉ ለሙሉ ማሳካት አልተቻለም፡፡

የውሳኔዎችን ተፈፃሚነት በማረጋገጥ የተገልጋዩን አመኔታ ከማሳደግ አንፃር በተጣለው ግብ መነሻነት ፍትሀዊና ውጤታማ ውሳኔዎችን በመስጠት፣ የተሰጡ ውሳኔዎች ተደራሽነትና ተፈፃሚነትን በመከታተልና የመረጃ ልውውጥ በማድረግ፣ ለአፈፃፀም ማነቆ የሚሆኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ተገቢውን ድጋፍ በማድረግ፣ በመስተዳድር ም/ቤት ፀድቀው የሚታተሙ ደንቦችን በማሳተም ለተገልጋዮች ተደራሽ በማድረግ፣ የተላለፉ ውሳኔዎችን ለሚመለከታቸው አካላት በቅልጥፍናና በጥራት በማደራጀት ተደራሽ በማድረግ፤ በሴክተሩ የሚሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ፍትሀዊነት፣ ውጤታማነትና የተገልጋዩን አመኔታ ያስገኙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በ2012 በጀት ዓመት ከነበረው የዕቅድ መነሻ 82.5% በ2015 በጀት ዓመት ወደ 88% ለማሳደግ ግብ ተጥሎ የዕቅዱን 83% ማሳካት የተቻለ ቢሆንም በክልል የተወሰኑ ውሳኔዎች በታችኛው መዋቅር ተፈፃሚ ያለመሆንና የቅንጅታዊ አሰራር ክፍተቶች በመኖራቸው ዕቅዱን ሙሉ በሙሉ መፈፀም አልተቻለም፡፡

ለሚቀርቡ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ምላሽ በመስጠት የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ከማሳደግ አንጻር በዕቅድ ዘመኑ በቅሬታ አፈታትና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የህብረተሰቡን ተሳትፎ በማሳደግ፣ የሪፎርም ተግባሪ ተቋማትን በመከታተልና በመደገፍ፣ ለፀጥታ ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ በመስጠት፤ በቅሬታና አቤቱታ መንስኤዎችና መፍትሄዎቻቸው ዙሪያ ጥናት በማካሄድ ቅሬታና አቤቱታዎችን በመቀነስ፣ በቅሬታ አፈታትና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ መሳተፍ የሚገባቸው አካላትን በማሳተፍ እንዲሁም በጥናት ሰነዱ በተቀመጠው መሰረት ትንታኔ ተሰርቶ ከመፍትሄ ሀሳብ ጋር መረጃዎችን የማቅረብ ሥራዎችን ለመስራት

በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 82.5% በ2015 በጀት አመት ወደ 88% ለማድረስ ታቅዶ የዕቅዱን 83% ማሳካት የተቻለ ቢሆንም የጥናት ሰነዶቹን በታቀደው ልክ ማዘጋጀት አለመቻሉ፣ የሪፎርም ተግባሪ ተቋማት በፕሮግራሞቹ ላይ ያላቸው ትኩረት አናሳ መሆን እና ከሀገራዊ ወቅታዊ ሁኔታ ጋር ተያይዞ በታቀደው ልክ ውጤት ሊመጣ አልቻለም፡፡

የበጀትና ፊዚካል ዕቅድ አፈፃፀም ውጤታማነትን ከማረጋገጥ አንፃር በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 1፡80 በ2015 በጀት ዓመት 1፡1 ለማድረስ ታቅዶ የዕቅዱን 1፡90 ማድረስ የተቻለ ቢሆንም በዕቅድ የተያዘ በጀትን ለታቀደው ተግባር ከማዋል አኳያ ክፍተቶች ያሉበትና እንደተቋሙ ባህሪይ በደራሽ ሥራዎች/በፀጥታና ወቅታዊ ጉዳይ/ ዕቅድን መሰረት ያደረገ የበጀት አጠቃቀም ያለመኖር ችግሮች በቀጣይ የዕቅድ ዝግጅትና ትግበራ ዘመን እንደተቋም ተይዞ መመራት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡

የአገልግሎት አሠጣጥ ጥራትና ቅልጥፍናን ከማሰደግ አንጻር የአሰራር ስርዓትና ውጤት ተኮርን በመተግበር፣ በተቀመጡ ስታንዳርዶች ስራዎችን በማከናወን፣ ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር፣ የካቢኔ ስብሰባ ሂደቶችን በማመቻቸትና የተቀረፀ አጀንዳ በቅልጥፍና ለካቢኔ አባላት ተደራሽ የሚደረግበትን ቀን በማሳጠር፣ ቃለ ጉባኤዎችን በአግባቡ በመያዝና በማደራጀት፤ መረጃ በመሰብሰብና የትንታኔ ስራዎችን በመስራት እንዲሁም የህብረተሰብ ተሳትፎን በማሳደግ የአገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል፣ ከሴክተሮች በሚሰበሰቡ ዕቅዶችና የአፈፃፀም ሪፖርቶች ላይ ሙያዊ አስተያየት በመስጠት በተቀመጡ ቀናት አጠናቅሮ ለውሳኔ የማቅረብ ስራ ላይ እንዲውሉ፣ በቢሮ ውስጥ በስልክ እና በመስክ የሚጣሩ የሪፎርምና ፀጥታ ጉዳዮች፣ ቅሬታዎች፣ አቤቱታዎችና ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮችን አጣርቶ ለሚመለከተው አካል የውሳኔ ሀሳብ ለማቅረብ በ2012 በጀት አመት ከነበረበት 80% በ2015 በጀት ዓመት 100% ለማድረስ ታቅዶ የዕቅዱን 92% ማሳካት የተቻለ ቢሆንም የአስፈጻሚ ሴክተር መ/ቤቶች ዕቅድና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን በወቅቱና በጥራት ባለማቅረባቸው፣ የካቢኔ አጀንዳዎች በወቅቱ ያለመድረስ፣ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓቱ ደካማ መሆንና ሥራዎችን በስታንዳርድ መሰረት መፈፀም አለመቻል እንደክፍተት ተገምግሟል፡፡

የፕሮቶኮል አገልግሎት ሽፋንን በማሳደግ የተገልጋዩን አመኔታ ለማረጋገጥ ከተጣለው ግብ አንጻር በበጀት ዓመቱ ከፌዴራል መንግስት፣ ከአቻ ክልሎች፣ ከውጭ ሀገር የመጡ አምባሳደሮችና በሀገር ውስጥ ላሉ የውጭ ሀገር ዲፕሎማቶች እና ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች የተሟላ የፕሮቶኮል አገልግሎት ሽፋን ከመስጠት ረገድ በ2012 በጀት አመት የነበረውን 100% አፈጻጸም በ2015 በጀት አመት አጠናክሮ ለማስቀጠል የተያዘው ዕቅድ መሉ በሙሉ ወቅቱን በጠበቀ ሁኔታ በአግባቡ ተከናወኗል ፡፡

የሴክተሩን የማስፈፀም አቅም ከማሳደግ አኳያ ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት የፈፃሚዎች እና የአስፈፃሚዎችን ብቃት ለማሳደግ የልምድ ልውውጦች እና አጫጭር የሥራ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን በመስጠት፣ የሚገኙ የትምህርት እድሎችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ፣ የሴክተሩን የመረጃ አደረጃጀት፣ አያያዝና አጠቃቀም በዘመናዊ ቴክኖሎጅ መሳሪያዎች በመታገዝ እንዲሰሩ በማድረግ እና የመረጃ ልውውጥ ሥርዓቱን በማሻሻል በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 73.5% በ 2015 በጀት ዓመት 88% ለማድረስ ታቅዶ 76% ለማሳካት ጥረት የተደረገ ሲሆን በየደረጃው ለሚገኙ ፈጻሚዎችና አመራሮች

በቂ ስልጠና አለመሰጠቱ፣ በቂ የልምድ ልዉዉጥ አለመኖር፣ በቴክኖሎጂ የመጠቀም ልምድ ማነስ፣ በቴክኖሎጂ መሳሪያዎች የተያዘ የመረጃ አያያዝ ክፍተት መኖሩ እንደጉድለት ተገምግሟል፡፡

የዕቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ጥራትን ከማሳደግ አንጻር በሴክተሮች የሚከናወኑ ዕቅዶችና ፕሮጀክቶችን፣ በሴክተሩ በሁሉም ዞኖችና ልዩ ወረዳዎች ክትትልና ድጋፍ በማድረግ፣ በተሰጡ ውሳኔዎች ተፈፃሚነት ላይ ክትትል በማድረግ፣ሙያዊ የህግ ድጋፍና የማማከር አገልግሎትን በመስጠት እና በአስፈጻሚ መ/ቤቶች የሚደረግ ድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ ሽፋንን በ2012 አንድ ጊዜ ወይም 25% ከነበረበት በ2015 በጀት አመት አራት ጊዜ (100 %) ክትትል ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ ሁለት ጊዜ ወይም የዕቅዱን (50 %) መፈፀም የተቻለ ቢሆንም በ2013፣ 2014 እና 2015 ዓ/ም የነበረው የክትትልና ድጋፍ ሥራ በአለማቀፍ ደረጃ የተከሰተው የኮቪድ ወረርሽኝ፣ ሀገራዊ ለውጡን ተከትሎ በተፈጠሩ የፀጥታ ችግሮችና አለመረጋጋት፣ በየአካባቢው በሚነሱ የመዋቅር ጥያቄዎች ምክንያት ከታችኛው መዋቅር ጋር በተፈጠረ የግንኙነት መላላት ተናቦ ለመስራት አለመቻል፣ ምክንያት በተለይም በመስክ የሚደረጉ የድጋፋዊ ክትትል ሥራዎች በታቀደው መሰረት ባለመከናወናቸው ዕቅዱን በተፈለገው ልክ ማሳካት አልተቻለም፡፡

# ክፍል ሶስት

## 3. የሴክተሩ መሪ ዕቅድ መነሻዎች፣ ዓላማዎች፣ ግቦችና የትኩረት አቅጣጫዎች

### 3.1. መነሻዎች

ዕቅዱ ሲዘጋጅ መነሻ የተደረጉ ዋና ዋና ጉዳዮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ያለፉት አስር ዓመታት የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ እና ከ2013-2015 ዓ.ም ያለው የስትራቴጂክ ዕቅድ አፈፃፀም ውጤት፤
- የክልሉ ህዝብ የልማትና የመልካም አስተዳደር ፍላጎት፤
- የመንግሥት የትኩረት አቅጣጫዎች፣
- ሀገራችን የደረሰችበት የቴክኖሎጂ እድገትና አጠቃቀም እና
- ወቅታዊና ነባራዊ ሁኔታን መሰረት በማድረግ የተጣሉ ሀገራዊ ግቦች ለመሪ ዕቅዱ ዝግጅት እንደ መነሻ ተወስዷል፡፡

### 3.2. የዕቅዱ ዓላማ

#### 3.2.1. ዋና ዓላማ (General Objective)

- የሴክተሩን ተልዕኮ ለማሳካት የሚያስችሉ ተግባራትን ስትራቴጂክ በሆነ መንገድ በመምራት በክልሉ ሁለንተናዊ እድገት በማምጣትና እና መልካም አስተዳደር በማስፈን የክልሉን ህዝቦች ፍትሀዊ ተጠቃሚነትና ብልፅግና ማረጋገጥ ነው፡፡

#### 3.2.2. ዝርዝር ዓላማዎች (Specific Objectives)

- አስተዳደር ሴክተሩ የተሰጠውን ተግባርና ሃላፊነት በብቃት መወጣት እንዲችል ለማድረግ፣
- በየደረጃው በሚገኙ የአስተዳደር እርከኖች የተደራጀውን ተቋማዊ መዋቅር የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ለመገንባት፣
- ሴክተሩ ለተገልጋይ የሚሰጠውን አገልግሎት ፍትሀዊ፣ ቀልጣፋ፣ ተደራሽና ጥራት ያለው ለማድረግ፣
- ተቋሙ ያለውን ውስን ሀብት ውጤታማ በሆነ አግባብ ለመምራት እንዲቻል፣
- ክልሉ ሰላምና ፀጥታ የሰፈነበትና ለልማት ምቹ እንዲሆን ለማስቻል፤

### 3.3.የዕቅዱ አስፈላጊነት

- በግቦችና ተግባራት መካከል ትስስር ለመፍጠር፤
- ተጠያቂነት ያለበት አሰራርን ለማስፈን፣
- ሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብትን አቀናጅቶ በመምራት ውጤታማነትን ለማረጋገጥ፣
- ውጤትን መሰረት ያደረገ ምዘና ለማካሄድ፤
- ተዋረዳዊና የጎንዮሽ ግንኙነቶችን ለማጠናከር፣
- በተቋሙና በባለድርሻ አካላት መካከል ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር፤
- የተቋሙን ተልዕኮ ለማሳካትና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ፤
- የክልሉን ህዝብ የልማት ፍላጎት ለማሟላትና የሚስተዋሉ የመልካም አስተዳደር ተግዳሮቶችን ለመፍታት
- ተቋማዊ ዉጤታማነትን በማሳደግ የህብረተሰቡን እርካታ ለማረጋገጥ፤

### 3.3. የዕቅዱ ወሰን

መሪ ዕቅዱ ከ2016-2022 በጀት ዓመት ተግባራዊ የሚደረግ ሆኖ በክልል፣ በዞኖችና በልዩ ወረዳዎች ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ ዞኖችና ልዩ ወረዳዎችም ይህንን ዕቅድ መነሻ በማድረግ ከራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር የየራሳቸውን መሪ ዕቅድ የሚያዘጋጁ ይሆናል፡፡

### 3.4. የትኩረት መስኮች

| ተ.ቁ | ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች | ስትራቴጂያዊ ውጤቶች |
|---|---|---|
| 1 | ክትትል፣ድጋፍ፤መግምገማና | ዉጤታማ የዕቅድ አፈጻጸምና ውሳኔ |
| 2 | መልካም አስተዳደር | የጎለበተ የግልጸኝነትና የተጠያቂነት አሰራር |
| 3 | የመስተዳድር ምክር ቤት ጉዳዮች | ዉጤታማ የመረጃ ልዉዉጥና የተሳለፉ ዉሳኔዎች |

#### 3.4.1.የተመረጡ የትኩረት መስኮችና ማብራሪያዎች፣

**1. ክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማና ማማከር**

**ውጤት፡- ዉጤታማ የዕቅድ አፈጻጸምና ውሳኔ**

የሴክተር መስሪያ ቤቶችን ዕቅዶች ለማሳካት የተቀመጡ ስትራቴጂክ ግቦች ከሀገራዊና ክልላዊ ፖሊሲዎች፣ፕሮግራሞች፣ ስትራቴጂዎችና ፕሮጀክቶች አንፃር ተቃኝተው የተዘጋጁ መሆናቸውን የመገምገም፣ አፈፃፀማቸውን የመከታተል፣ የመደገፍና ግብረ-መልስ የመስጠት እና ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮችን አጣርቶ የማቅረብና የማማከር ሥራዎችን በመስራት የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ስለሚጠበቅበት **"ክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማና ማማከር"** አንድ የትኩረት መስክ ሆኖ

ተመርጧል፡፡ በመሆኑም ክትትል፣ ድጋፍ፣ ግምገማና ማማከር አንድ የትኩረት መስክ ሆኖ ሲመረጥ፡-

- ግቦች ከፖሊሲዎችና ከፕሮግራሞች አንፃር ተቃኝተው ስለመዘጋጀታቸው የመገምገምና የማረጋገጥ፤
- ውሳኔ በሚሹ ጉዳዮች ላይ የማማከር፤
- ዕቅዶች ከተቀመጡ ግቦች አንፃር እየተቃኙ እየተፈፀሙ ስለመሆናቸው የመከታተል፣ የመደገፍ፣ የመገምገምና ግብረ-መልስ የመስጠት፤
- የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች የመገምገም፣ የማጠናቀርና ለሚመለከተው አካል የማቅረብ እና
- በክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ ሂደት የተለዩ የአሰራር ክፍተቶች እንዲሻሻሉ አስተያየት የማቅረብ ሥራ የሚሰራበት መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡

**2.መልካም አስተዳደር**

**ውጤት፡- የጎለበተ የግልጸኝነትና የተጠያቂነት አሰራር**

በቅሬታ መንስኤዎችና መፍትሄዎች ላይ ጥናት የማድረግ፤ የሪፎርም ማሻሻያ ፕሮግራሞች በተሳለጠ መንገድ እንዲተገበሩ የማድረግ፤ አስተዳደራዊ ቅሬታዎችንና አቤቱታዎችን የመፍታት፤ ክልሉ ሰላም፣ ፀጥታና ፍትህ የሰፈነበትና ለልማት ምቹ እንዲሆን የማስተባበር እንዲሁም መልካም አስተዳደርን ለማረጋገጥ በሚከናወኑ ተግባራት ላይ የፈፃሚውና የህብረተሰቡ ግንዛቤ እንዲያድግ የማድረግ ሥራዎችን ለመስራት **መልካም አስተዳደር** አንዱ የትኩረት መስክ ሆኖ ተመርጧል፡፡ በመሆኑም **መልካም አስተዳደር** የትኩረት መስክ ሆኖ ሲመረጥ፡-

- የቅሬታና አቤቱታ መንስኤዎችንና መፍትሔዎቻቸውን በጥናት የመለየት፤
- አስተዳደራዊ ቅሬታዎችንና አቤቱታዎችን የመፍታት፤
- የሪፎርም ፕሮግራሞችና ፓኬጆች በተሳለጠ መንገድ እንዲተገበሩ የማድረግ፤
- በመልካም አስተዳደር ዙሪያ የህብረተሰቡ ግንዛቤ እንዲጎለብት የማስተባበር፤
- የህብረተሰቡ ሰላምና ፀጥታ እንዲረጋገጥ የማስተባበር፣ ከሚመለከታቸው የፌደራልና አጎራባች ክልሎች ጋር በጋራ የመስራት፤
- በመስተዳድር ምክርቤቱ እንዲፀድቁ የሚላኩ ረቂቅ የህግ ማዕቀፎችን አግባብነት የማጣራት፣
- የመስተዳድር ምክርቤቱን አሰራር ለማሻሻል የሚረዱ ውስጠ ደንቦችና መመሪያዎችን እንዲዘጋጁ ሙያዊ ድጋፍ የማድረግ፣

- በተሟላ መረጃና ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ሙያዊ የህግ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት የመስጠት፣
- በህግ ጥላ ስር የሚገኙ ታራሚዎች የሚያቀርቡትን የይቅርታ ጥያቄ ተገቢነት የማጣራት፣
- የታራሚዎችን ሰብአዊ መብት አያያዝ የመከታተል፣
- በአጠቃላይ በሪፎርም፣ በፀጥታ እና በህግ ጉዳዮች ዙሪያ የማማከር ተግባር ያከናዉናል፡፡

**3.የመስተዳድር ምክር ቤት ጉዳዮች**

**ውጤት ፡- የጎለበተ የማስፈፀም አቅም፣ ዉጤታማ የመረጃ ልዉዉጥና የተላለፉ ዉሳኔዎች**

ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራርን የማጎልበት፤ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርጉ የህግ ማዕቀፎች እንዲወጡ የማስተባበር፤ የመስተዳድር ምክር ቤት ውሳኔዎችን ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ የማድረግ፤ ሰነዶችን አደራጅቶ የማስቀመጥ፤ ለተለያዩ የትብብርና የድጋፍ ጥያቄዎች ምላሽ የመስጠት ሥራዎችን በመስራት ዉጤታማ የመረጃ ልዉዉጥና የዉሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት እንዲኖር የማድረግ ፣ ለፌደራል፣ ለክልሎች፣ ለክልሉ የበላይ አመራር አካላት፣ በሀገር ውስጥ ለሚገኙ ዲፕሎማቶች፣ ከውጭ ሀገር ለሚመጡ አምባሳደሮች እና እንግዶች የፕሮቶኮል ሽፋን አገልግሎት የመስጠት ተግባራትን ለማከናወን **የመስተዳድር ምክር ቤት ጉዳዮች** የትኩረት መስክ ሆኖ ተመርጧል፡፡ በመሆኑም **የመስተዳድር ምክር ቤት ጉዳዮች** የትኩረት መስክ ሆኖ ሲመረጥ፡-

- የካቢኔ የስብሰባ ሂደቶችን የማመቻት፤
- የመስተዳድር ም/ቤቱን ውሳኔ የሚሹ የኢንቨስትመንትና የምትክ መሬት ጥያቄዎችን አደራጅቶ የማቅረብ፤
- የካቢኔ ውሳኔዎችን ተደራሽ የማድረግ፤
- የህግ ማዕቀፎችን እንዲዘጋጁና እንዲፀድቁ የማስተባበር፤
- በመስተዳድር ም/ቤቱ የፀደቁ ደንቦችንና መመሪያዎችን አደራጅቶ የማሳተምና የማሰራጨት፤
- የመስተዳድር ም/ቤቱን ሰነዶች የማደራጀትና በጥንቃቄ የመያዝ፤
- በመስተዳድር ም/ቤቱ ታይተው ውሳኔ የተሰጠባቸው አዋጆች እንዲፀድቁ ለክልሉ ም/ቤት አደራጅቶ የመላክ፤
- የርዕሰ-መስተዳድሩንና የምክትል ርዕሰ-መስተዳድሮችን የስብሰባና የጉብኝት ፕሮግራሞችን የማቀናጀትና የማረጋገጥ፤

- ለርዕሰ መስተዳድሩ፣ ለምክትል ርዕሰ መስተዳድሮች፣ ለፌደራል፣ ለክልሎች፣ በሀገር ውስጥ ለሚገኙ ዲፕሎማቶች፣ ከውጭ ሀገር ለሚመጡ አምባሳደሮች እና እንግዶች የፕሮቶኮል ሽፋን አገልግሎት የመስጠት፤
- የርዕሰ መስተዳድሩንና የምክትል ርዕሰ-መስተዳድሮችን የውጭ ሀገር ጉዞዎችን የማመቻቸት እና ርዕሰ-መስተዳድሩ በተለያዩ ኩነቶች የሚሰጧቸውን መግለጫዎች የማስተባበርና የማመቻቸት ሥራዎች የሚሰሩበት መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡

## 3.5. የዕቅዱ ግቦች

- ❖ ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራርን ማጎልበት፣
- ❖ ፈጣንና ፍትሃዊ ውሳኔ በመስጠት የተገልጋዩን እርካታ ማሳደግ፤
- ❖ ለሚቀርቡ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ምላሽ በመስጠት የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማሻሻል፤
- ❖ የውሳኔዎችን ተፈፃሚነት በማረጋገጥ የተገልጋዩን አመኔታ ማሳደግ፤
- ❖ ውጤታማ የመረጃ ሥርዓትን በማስፈንና የዉሳኔ ጥራትን በማረጋገጥ የተገልጋዩን ተጠቃሚነት ማሳደግ፤
- ❖ የፕሮቶኮል አገልግሎት ሽፋንን ማሳደግ፤
- ❖ የዕቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ጥራትን ማሳደግ፤

## 4. የሴክተሩ ስትራቴጂያዊ ግቦች

| ግቦች | የግብ ወሰን | የግብ ስኬት |
|---|---|---|
| ተቋማዊ የማስፈጸም አቅም፣ የሀብት አጠቃቀም እና የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራርን ማጎልበት | ❖ የተመደበ በጀትና ሀብት ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ የተቀመጠ ግብ ነው፡፡<br>❖ የፈፃሚዎችን አቅም በማጎልበት፣ **የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በማዘመንና** ተቋማዊ ባህልን በመገንባት የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል የተጣለ ግብ ነው፡፡ | ያደገ የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነት<br>የተሻሻለ አሰራር<br>የተሻሻለ አፈፃፀም |
| ፈጣንና ፍትሃዊ ውሳኔ በመስጠት የተገልጋዩን እርካታ ማሳደግ፣ | ፈጣን አገልግሎትና ውሳኔ በመስጠት ተገልጋዩን ለማርካት ታስቦ የተጣለ ግብ ነው፡፡ | • ያደገ የተገልጋይ እርካታ |
| የውሳኔዎችን ተፈፃሚነት በማረጋገጥ የተገልጋዩን አመኔታ ማሳደግ፣ | በተሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበራቸውን በመከታተል፣ በመገምገምና በመደገፍ ህብረተሰቡ በተቋሙ ላይ ያለውን አመኔታ ለማሳደግ የተጣለ ግብ ነው፡፡ | • ያደገ የተገልጋይ አመኔታ |
| ለሚቀርቡ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ምላሽ በመስጠት የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማሻሻል፣ | ለቀረቡ የልማትና አስተዳደራዊ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ተገቢውን ምላሽ በመስጠት የኅብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ታስቦ የተጣለ ግብ ነው፡፡ | • ያደገ የህብረተሰብ ተጠቃሚነት |
| ውጤታማ የመረጃ ሥርዓትን በማስፈንና የዉሳኔ ጥራትን በማረጋገጥ የተገልጋዩን ተጠቃሚነት ማሳደግ፤ | ከህብረተሰቡና ከተቋማት የሚቀርቡ መረጃዎችን ተገቢነት በመመርመር ጥራት ያለው ውሳኔ እንዲሰጥ በማድረግ ህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ታስቦ የተጣለ ግብ ነው፡፡ | • ያደገ የህብረተሰብ ተጠቃሚነት |
| የፕሮቶኮል አገልግሎት ሽፋንን በማሳደግ የተገልጋዩን አመኔታ ማረጋገጥ፣ | የመንግስት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎችና ዲፕሎማቶች ብቃትና ጥራት ያለው የፕሮቶኮል ሽፋን በመስጠት የገጽታ ግንባታን ለማረጋገጥ የተጣለ ግብ ነው፡፡ | • ያደገ የተገልጋይ አመኔታ |
| የዕቅድ አፈፃፀም ክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ ጥራትን ማሳደግ፤ | የአስፈፃሚ መ/ቤቶችን ዕቅድ በመገምገምና በማረጋገጥ የዕቅድ አፈፃጸም ድጋፋዊ ክትትል በማድረግና ግብረመልስ በመስጠት ተቋማት የተሻለ አፈፃፀም እንዲኖራቸው ታስቦ የተጣለ ግብ ነው፡፡ | • ያደገ የዕቅድ አፈፃፀም ጥራት<br>• የጎለበተ ቅንጅታዊ አሰራር |

## 5.የሴክተሩ የሰባት ዓመት ዕቅድ የድርጊት መርሃ ግብር

| ግቦች | መለኪያዎች | መግለጫ | መነሻ አፈፃፀም | ዒላማ/ታርጌት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| ፈጣንና ፍትሃዊ ውሳኔ በመስጠት የተገልጋዩን እርካታ ማሳደግ፣ | የተገልጋይ ዕርካታ በመቶኛ | በሴክተሩ አገልግሎት ካገኙ ተገልጋዮች ውስጥ እርካታቸውን የገለጹትን ቁጥር ለአጠቃላይ ምላሽ ሰጭዎች ቁጥር በማካፈል በመቶኛና የተገልጋይ እርካታ ዳሰሳ ጥናት ውጤትን በማስላት ይሆናል። | 80.5 % | 89 | 90 | 90 | 92 | 93 | 94 | 95 |
| የውሳኔዎችን ተፈፃሚነት በማረጋገጥ የተገልጋዩን አመኔታ ማሳደግ፣ | አመኔታው የጨመረ ህብረተሰብ በመቶኛ | የተሰጡ ውሳኔዎችን መዝግቦ በመያዝ ተፈፃሚነታቸውን በመከታተልና በመቶኛ በማስላት ይሆናል። | 83 % | 90 | 90 | 92 | 94 | 96 | 98 | 100 |
| ለሚቀርቡ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ምላሽ በመስጠት የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማሻሻል፣ | ምላሽ የተሰጣቸው ጥያቄዎችና ቅሬታዎች በመቶኛ | ከቀረቡ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች መካከል አግባብነታቸው ታይቶ ምላሽ የተሰጣቸውን በመለየትና በመቶኛ በማስላት ይሆናል። | 83 % | 90 | 90 | 92 | 94 | 96 | 98 | 100 |
| የፕሮቶኮል አገልግሎት ሽፋንን በማሳደግ የተገልጋዩን አመኔታ ማረጋገጥ፣ | የተሰጡ የፕሮቶኮል ሽፋኖች በመቶኛ | ብቃትና ጥራት ያለው የፕሮቶኮል ሽፋን በመቶኛ | 100% | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የሴክተሩን የማስፈጸም አቅም ማጎልበት | የተሻሻለ የሰው ሀብት ልማት እና አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት በመቶኛ | ስልጠናዎችና የትምህርት እድሎች እና የልምድ ልውውጦች በመቶኛ የሚሰላ ይሆናል | 76 % | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

| ግቦች | መለኪያዎች | መግለጫ | መነሻ አፈፃፀም | ዒላማ/ታርጌት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 |
| | | በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደራጁና በጥቅም ላይ የዋሉ መረጃዎች በመቶኛ የሚሰላ ይሆናል | | | | | | | | |
| የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ | የተሻሻለ የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር አሰራርና ውጤታማነት ንፅፅር በመቶኛ | በየበጀት አመቱ የተመደበ በጀትና የፊዚካል ዕቅድ ክንዉንን በማነጻጸር፣ የግዥ፣ ክፍያና ንብረት አያያዝና አፈፃፀምን በመቶኛ የሚሰላ ይሆናል | 1:90 | 1:95 | 1:1 | 1:1 | 1:1 | 1:1 | 1:1 | 1:1 |
| የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትና ቅልጥፍናን ማሳደግ | የዕቅድና የአፈጻጸም ሪፖርት፣ የካቢኔ አጀንዳ በጥራት አጠናቅሮ ማቅረቢያ በመቶኛ | ከሴክተሮች የሚሰበሰቡ እቅዶችና የአፈፃጸም ሪፖርቶች፣ ግምገማ ውጤት የተሰጡ የፕሮቶኮል አገልግሎት ሽፋን፣ የካቢኔ አጀንዳ ጥራትና ተደራሽነት፣ የሪፎርምና ፀጥታ ጉዳዮች፣ ቅሬታዎች፣ አቤቱታዎችና ውሳኔ የሚሹ ጉዳዮችን አጣርቶ ውሳኔ የመስጠት አፈፃፀምን በመቶኛ የሚሰላ ይሆናል | 92 % | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የዕቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ጥራትን ማሳደግ፣ | የተደረገ ክትትልና ግምገማ ሽፋን በዙር | በፕሮጀክቶች፣ በሴክተሮች፣ በየደረጃው በሚገኙ የአስተዳደር እርከኖች በሚደረግ ድጋፋዊ ክትትልና ግምገማ ሽፋን በመቁጠር የሚሰላ | 2 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 |

# ክፍል አራት

# 4. የማስፈፀሚያ ተቋማዊ አቅም ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች

## 4.1. የማስፈፀሚያ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች

### 4.1.1. መሪ ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ምቹ ሁኔታዎች

- መንግስት ለአሰራር ማነቆ የሆኑ ህጎችን ለማሻሻል ያለው ቁርጠኝነት፣
- ዜጎች በሀገራቸው ጉዳይ ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚያስችል የፖለቲካ ምህዳር መስፋት፣
- የሕግ አውጪው፣ የሕግ አስፈፃሚውና የሕግ ተርጓሚው ተግባር በየደረጃው ተለይቶ በሕግ መቀመጡ፣
- የአስፈፃሚ አካላት አደረጃጀት ሊያሰራ በሚያስችል መልኩ በመዋቅራዊ ሪፎርም መቃኘቱ፣
- ሀገራዊ የኢኮኖሚ ሪፎርም እየተደረገ መሆኑ፣
- በክልሉ ምቹ ሥነ-ምህዳር ፣ የተፈጥሮ ሀብት፣ የሰው ሀይል፣ የአየር ንብረት ያለ መሆኑ፣
- ማህበራዊ ልማት ለማምጣት የሚያስችሉ ፖሊሲዎችና ኘሮግራሞች ተነድፈው በመተግበር ላይ መሆናቸው፣
- ማህበራዊ ችግሮችን በመቅረፍ ዙሪያ የህብረተሰቡ ግንዛቤ እየጨመረ መምጣቱ፣
- የሲቪክ ማህበራትን ተሳትፎ ለማጠናከር ማሻሻያዎች መደረጋቸው፣
- ለልማት አጋዥ የሆኑ ባህላዊና ማህበራዊ እሴቶች መኖራቸው፣
- ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ መምጣቱ፣
- የመሰረተ ልማት ተደራሽነት መሻሻል፣
- ከአጎራባች ክልሎች ጋር ያለው የትብብር ግንኙነት እየተጠናከረ መምጣቱ፣
- በክልሉ ለልማት ምቹ የሆነ አካባቢና ሰፊ የሰው ኃይል እንዲሁም ልዩ ልዩ የተፈጥሮ ሃብቶች መኖር፣

### 4.1.2. በዕቅዱ አፈፃፀም ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ሥጋቶች

- የህግ የበላይነትን ከማስከበር አንፃር ክፍተት መኖሩ፣
- በህዝቡ የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴ ላይ የደህንነት ስጋት መኖሩ፣
- መልኩን የቀየረ ሌብነት እየተስፋፋ መሆኑ፣
- የመልካም አስተዳደር ስርዓት ግንባታ ሥራ በሚፈለገው መጠን ውጤታማ ያለመሆኑ፣
- ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት መኖር
- የህዝብ ቁጥር መጨመር
- የአየር ፀባይ መለዋወጥ፣

- ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል ያለመኖሩ፣
- የሰራተኛው ገቢ ያለማደግ
- ምርትና ምርታማነት መቀነስ
- ኢኮኖሚው በሚፈለገው መልኩ የስራ ዕድል እየፈጠረ አለመሆኑ
- ህገ-ወጥ ንግድና ኮንትሮባንድ መስፋፋቱ፣
- ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ሙሉ በሙሉ አለመቀረፋቸው፣
- ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር መኖር፣
- የሥራ አጥነት መስፋፋት፣
- የህብረተሰቡ የስራ ባህል መዳከም፣
- ማህበራዊ ተቋማት መልካም ሥነ-ምግባር ያለውን ዜጋ ከማፍራት አንፃር ሚናቸው ያነሰ መሆኑ፣
- ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በአግባቡ ለመጠቀም የክህሎትና የሐብት ውስንነት መኖር፣
- የማህበራዊ ሚዲያ የግንኙነት መንገዶች በህብረተሰቡ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማሳደራቸው፣
- ለክልሉ አጎራባች በሆኑ ክልሎች ውስጥ የሚስተዋሉት ያልተረጋጋ የፀጥታ ሁኔታ መኖር፣

## 4.2. ስትራቴጂያዊ ዕርምጃዎች

ስትራቴጂያዊ ዕርምጃዎች በተቋም አፈፃፀም መነሻ እና በተቀረፁ ኢላማዎች መካከል ያለውን ክፍተት ለመሙላት የሚቀረፁ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶችና ፓኬጆች ሲሆኑ ለሚቀጥሉት ሰባት አመታት ሴክተሩ ከሚወስዳቸው ተቋማዊ እርምጃዎች፣ የህግ ጉዳዮች እርምጃዎችና የፖሊሲ እርምጃዎች የሆኑትንና በስትራቴጂያዊ እርምጃነት ሊወሰዱ የሚችሉ ዋና ዋና ጉዳዮች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡፡

- የአስተዳደራዊ ውሳኔዎችን ተፈፃሚነት ለመከታተል የሚረዳ አስተዳደራዊ ህግ መዘጋጀት፣
- በርዕሰ መስተዳድር የሚደራጁ ጽ/ቤቶችን ለማቋቋም የሚረዳ ደንብ፣
- የሰራተኞች የሰዓት መቆጣጠሪያ የጣት አሻራ ማሽን፣
- በተቋሙ በጥናቱ የተመላከተው የሰው ሀይል በትምህርት ዝግጅትና በሙያ መስመር ሲሆን በስራ ላይ የሚገኘው በቀጣይ ለዕቅድ ዘመኑ ውጤታማነት በጥናት ሰነዱ የተመላከተውን የሰው ሀይል ማሟላት አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል፡፡

# ክፍል አምስት

## 5.የፋይናንስ ፍላጎት

ለቀጣይ ሰባት ዓመታት የመሪ ዕቅድ ዘመን ለተቋሙ የሚያስፈልገው የፋይናንስ ፍላጎት ሲተነተን ለመደበኛ ደመወዝ ብር 238,684,199.00፣ለካፒታል ደመወዝ 9,705,006.00 ሲሆን ለመደበኛ ስራ ማስኬጃ ብር 478,554,234.00 ለካፒታል ሥራ ማስኬጃ 151,976,544.00 ሲሆን በጠቅላላ ድምር ብር 878,919,983.00

ያስፈልጋል ተብሎ ይገመታል። ከዚህ በተጨማሪ ከዚህ እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ለማሳይት ተሞክሯል።

| ተ.ቁ | ዓ/ም | ደመወዝ | | ስራ ማስኬጃ | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መደበኛ | ካፒታል | መደበኛ | ካፒታል | |
| 1 | 2016 | 5,158,627.00 | 1,022,961.00 | 50,442,143.00 | 16,019,164.00 | 92,642,895.00 |
| 2 | 2017 | 27,674,490.00 | 1,125,257.00 | 55,486,357.00 | 17,621,080.00 | 101,907,184.00 |
| 3 | 2018 | 30,441,939.00 | 1,237,783.00 | 61,034,993.00 | 19,383,188.00 | 112,097,903.00 |
| 4 | 2019 | 33,486,133.00 | 1,361,561.00 | 67,138,492.00 | 21,321,507.00 | 123,307,693.00 |
| 5 | 2020 | 36,834,746.00 | 1,497,717.00 | 73,853,341.00 | 23,453,657.00 | 135,639,461.00 |
| 6 | 2021 | 40,518,221.00 | 1,647,489.00 | 81,237,575.00 | 25,799,023.00 | 149,202,308.00 |
| 7 | 2022 | 44,570,043.00 | 1,812,238.00 | 89,361,333.00 | 28,378,925.00 | 164,122,539.00 |
| **ድምር** | | **238,684,199.00** | **9,705,006.00** | **478,554,234.00** | **151,976,544.00** | **878,919,983.00** |

# ክፍል ስድስት

## 5. የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት

| ተ.ቁ | የጥንካሬና ድክመት ማሣያ ዋና ዋና ጉዳዮች | ጥንካሬ | ድክመት |
|---|---|---|---|
| 1 | የአሰራር ሥርአት አደረጃጀት | • አዲሱ የሥራ ምዘናና ደረጃ አሰጣጥ ስርዓት ተጠናቆ ወደ ትግበራ መገባቱ፣<br>• የአስተዳደር ሴክተሩ ከክልል እስከ ቀበሌ ድረስ ለአሰራር በሚያመች መልኩ መደራጀቱ እና ለተገልጋዩ ሕብረተሰብ ተደራሽ የሆነ አገልግሎት መስጠት እንዲቻል አብዛኛዎቹ ዳይሬክቶሬቶች እስከ ወረዳ መዘርጋታቸው፣ | • በአሠራር ሥርአት ለውጥ ጥናቱ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የተግባራት አፈፃፀም ላይ ውስንነት መኖር፣<br>• በሴክቴሩ የህግ ማዕቀፎችን አዘጋጅቶ ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ውስነንት መኖሩ (የአስተዳደር ህግ፤ደንብ፤ወዘተ)<br>• በአስተዳደር ሴክተሩ ያለው የድጋፋዊ ክትትል፣ ግምገማና ሪፖርት አቀራረብና ግብረ መልስ ስርዓቱ ጠንካራ ያለመሆን፣<br>▪ የልምድ ልውውጦች አለመደረጋቸው፣ |
| 2 | የአገልግሎት አሰጣጥ | • እስከ ቀበሌ ድረስ በሙሉ ጊዜ መንግስታዊ አገልግሎት እየተሰጠ መሆኑ፣<br>• ለተገልጋዩ ተደራሽና ቀልጣፋ አገልግሎት መስጠት መቻሉ፣ | • አገልግሎት አሰጣጡ ወደሚፈለገው የስታንዳርድ ደረጃ አለመድረስ፣ |
| 3 | የሰው ኃይል | • ሴክተሩ የተሰጠውን ተልዕኮ ለመወጣት የሚያስችል ልምድና ብቃት ባለው የሰው ሃይል እንዲሟላ የዳይሬክቶሬት ጥናት ክለሳ መደረጉ፣ | • በሴክተሩ ባሉ ዳይሬክቶሬቶች ካለው የስራ ክብደትና ውስብስብነት አንፃር ተመጣጣኝ የሆነ የስራ ደረጃ አለመኖር፣<br>• የሰው ሀይል አለመሟላት፣ |
| 4 | የአመራር ብቃት | • አመራሩ የጋራ ራዕይ ያለው መሆኑ፣<br>• አመራሩ የተቋሙን ተልዕኮና ዓላማ ለማሳካት የሚያስችል ክህሎትና የሥራ ልምድ ያለው መሆኑ፣ | • የአመራሮች በደራሽ ሥራ መጠመድ፣<br>• የድጋፍ፣ ክትትልና ግብረ-መልስ ሥራ በተገቢው ትኩረት አለመምራቱ፣ |
| 5 | ስትራቴጂ | • የሴክተሩን ተልዕኮ እና ራዕይ በመቅረፅ፤ ስትራቴጂ በመንደፍ ተግባራዊ እንቅስቃሴ | • የሴክተሩ ተልዕኮና ራዕይ ስትራቴጂካዊ በሆነ አግባብ ከመመራት አንጻር |

| ተ.ቁ | የጥንካሬና ድክመት ማሣያ ዋና ዋና ጉዳዮች | ጥንካሬ | ድክመት |
|---|---|---|---|
| | | የተደረገ መሆኑ፣ | ውስንነት መኖሩ፤ |
| 6 | ፋሲሊቲዎች | • የዘመናዊ ቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን አቅርቦት እየተሟላ መሆኑ፣<br>• የተመቻቸ የስራ ክፍልና ማቴሪያሎችን ለማሟላት ጥረት መደረጉ፣ | • የዘመናዊ ቴክኖሎጂ መሳሪያዎች አጠቃቀምና አያያዝ ውስንነት መኖሩ፣<br>• ከተቋሙ ስፋት አንፃር የመሰክ ተሽከርካሪ በበቂ ሁኔታ አለመኖር |
| 7 | ተቋማዊ ባህል | • ለውጥ ፈላጊነት እና በውጤት የሚያምን አስተሳሰብ የበላይነትን እያገኘ መምጣቱ፣<br>• የአገልጋይነት ስሜት እየዳበረ መምጣቱ፣ | • ተሞክሮን የመቀመርና የማስፋት፣ ጥናትና ምርምር የማድረግ ባህል የሚፈለገው ደረጃ ላይ አለመድረስ፣ |
| 8 | ፋይናንስ | በታቀደ እቅድ መሰረት በጀት መደልደል መቻሉ፣ | • የተመደበን በጀት ለታቀደው ሥራ ከማዋል አንጻር ክፍተት መኖሩ፣<br>• ከግዢ አንጻር ወቅታዊነት ጋር ተያይዞ ክፍተት መኖር፣ |

## 6.2 የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት

**ክትትልና ግምገማ** እቅድን ውጤታማ ለማድረግ ከሚያስችሉ መንገዶች ውስጥ አንዱና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። ክትትል ተከታታይነት ባለው መልኩ መረጃ የሚሰበሰብበትና አፈፃፀሙን በታቀደው መሰረት ለማስኬድ እንደ አስፈላጊነቱ ድጋፍና ማስተካከያ የሚደረግበት ሲሆን ግምገማ ደግሞ በተወሰነ የጊዜ ገደብ የተከናወነውን ስራ ከዕቅድ ጋር በማነጻጸር እቅዱ ወጤት እያስገኘ መሆኑን ከተለያየ የመገምገሚያ መስፈርት አንፃር በተቻለ መጠን የግምገማ መርሆዎችን ማለትም፡- ግልጽነት፣ አሳታፊነት፣ ወቅታዊነትና ሚዛናዊነትን በተከተለ መልኩ የሚገመግምበትና ለቀጣይ አፈፃጸም ጠቃሚ ተሞክሮ የሚወሰድበት ሥርዓት ነው።

በመሆኑም በቀጣይ የሰባት አመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ዘመን (2016-2022) በአስተዳደር ሴክተሩ የክትትል፤ ድጋፍ፤ ግምገማና ማማከር፤ መልካም አስተዳደርና መስተዳድር ም/ቤት ጉዳዮች የትኩረት መስኮች ተመርጠዋል። ስለሆነም በዕቅድ ዘመኑ የሚጠበቀው ስትራቴጂያዊ ውጤት እንዲመጣ የጽ/ቤቱ ዋናና ደጋፊ ዳይሬክቶሬቶች እና በየደረጃው ያሉ የአስተዳደር ጽ/ቤቶች ከሴክተሩ ስትራቴጂያዊ ግቦች የራሳቸውን ድርሻ በመውሰድና በማዘጋጀት አፈጻፀሙን ቅንጅታዊ በሆነ መልኩ በማስተባበርና በመፈፀም በተጠያቂነትና በኃላፊነት መንፈስ ድርሻቸውን የተወጡትን በመለየት ለመለካትና የታዩ የአፈጻጸም ክፍተቶችን ለመሙላት የሚያስችል የክትትልና ግምገማ ስርዓት በሚከተለው መልኩ ተዘጋጅቷል፡-

**የክትትል ሥርዓት፡-** ሴክተሩ በስትራቴጂክ እቅድ ዘመኑ ለማከናወን የታቀዱ ተግባራትን በእቅዱ መሰረት እየተከናወኑ መሆናቸውን እንዲሁም ክንውኑ ተፈላጊውን ውጤት ማስገኘት መቻሉን ለመከታተልና በትግበራ ወቅት የሚያጋጥሙትን ችግሮች በመለየት በወቅቱ ለመፍታትና ማስተካከያ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ በየሩብ ዓመቱ የሚከናወን ይሆናል፡፡

**የግምገማ ሥርዓት፡-** ሴክተሩ በአፈጻጸም ወቅት የታዩ ክፍተቶችን እና ፈታኝ ሁኔታዎችን በመለየት በቀጣይነት የማስተካከያ እርምጃዎችን ለመውሰድ የስትራቴጂውን የሀብት አመዳደብና አጠቃቀም በቀጣይነት ለማሻሻል፣ የተለያዩ ፈጻሚ አካላትን በአፈጻጸም ውጤታቸው መሠረት ዕውቅና ለመስጠትና ለማበረታታት፣ ለሚቀጥለው የስትራቴጂ እቅድ ዘመን ለስትራቴጂ ቀረጻ ግብዓት የሚሆኑ ጉዳዮችን ለመለየት፣ ስለስትራቴጂው አፈጻጸምና ስለተገኘው ውጤት ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት መረጃ ለመስጠት ጠቃሚ በመሆኑ በዕቅድ ዝግጅት፣ በትግበራና በውጤት ማጠቃለያ ደረጃ ክትትልና ግምገማ የሚካሔድ ይሆናል፡፡

## 7.ማጠቃለያ

በአስተዳደር ሴክተሩ የአስር ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ በመንደፍ በዚሁ ስነድ ላይ የተመለከቱ ስትራቴጂካዊ ግቦችን በመጣልና በመተግበር ባለፉት ሦስት የዕቅድ አፈጻጸም አመታት አበረታች ውጤቶችን ለማስመዝገብ ተችሏል፡፡

በአፈፃፀም ሂደትም የተገኙ ተሞክሮዎችን በመፈተሽ የወቅቱን ውስጣዊና ውጫዊ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የትኩረት መስኮችና የአስተዳደር ሴክተሩን ግቦች በማካተት ለቀጣይ ሰባት ዓመታት ተግባራዊ ሊደረግ የሚችል መሪ ዕቅድ ለማዘጋጀት ተችሏል ፡፡

ለዚህ ዕቅድ ስኬትም አመራሩም ሆነ ሠራተኛው የዕቅዱን መሠረታዊ ጽንሰ-ሀሳብ በመረዳት ለክልሉ ኢኮኖሚያዊና ፣ማኀበራዊ ልማት የራሱን አሰተዋፅኦ ማበርከት ይጠበቅበታል ፡፡

በመጨረሻም በዕቅዱ የተካተቱትን ግቦች በተሳካ መልኩ ለማከናወን እንዲቻል የሚያስፈልገውን በጀት ለሥራ ተነሣሽ በሆነ የሰው ኃይል በመጠቀም ውጤታማ መሆን የሁሉን ያልተቆጠበ ጥረት የሚጠይቅ በመሆኑ ድርሻችንን አወቀን ወደ ተግባር ልንገባ ይገባል በማለት ይህ የሰባት ዓመት መሪ ዕቅድ ወቅታዊ ሁኔታዎችን በማካተት እንደገና ተሻሽሎ ተዘጋጀቷል ፡፡